# የዜሮ ድምር ፖለቲካ ዜሮነት በተግባር ሲረጋገጥ

**ዘአማን በላይ** bzaman@yahoo.com

በዛሬው ፅሑፌ ራስ ወይም ርዕስ ላይ ላነሳሁት አንኳር ጉዳይ ንፃሬ ይሆነኝ ዘንድ ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት በአዕምሮዬ ጓዳ ውስጥ የከተብኩትን አስገራሚ ክንዋኔ ለአፍታ አስታወስኩት። …አዎ! የዛሬ ሁለት ዓመት ትንሽ እልፍ ሲል እንዲህ ሆነ።…ግንቦት ሃያ ቀን 2003 ዓ.ም። በዓሉን ለማክበር እንዲሁም በፌስ ቡክ ሃሳባዊ ዓለም ላይ የአመፅ ጥሪን የቀመሩ ሰዎችን ምናልባት ካሉ ለመመልከት መስቀል አደባባይ ተገኝቻለሁ። አደባባዩ ጠጠር መጣያ የለውም—ከአፍ እስከ ገደፉ ጢም ብሏል። ካለሁበት ቦታ ሆኜ በአሻጋሪ ወደ "ሜክሲኮ" አቅጣጫ አማተርኩ—ህዝቡ ይጎርፋል፡፡ …

…አብዛኛው ህዝብ "ዓባይን ለልማት በማዋል ከድህነት እንላቀቃለን!" የሚል መፈክር ይዟል።…እርግጥ በሃያሉ ግንቦት ሃያ ቀን በሃሳባዊ የኢንተርኔት ቅኝት ዓለም ውስጥ ሁከት ለመቀስቀስ ያለሙ ተስፈኞች፤ በኢትዮጵያ ህዝቦች የድል ቀን ዓይናቸው ደም የሚለብስ፣ ፌስ ቡክ ላይ ሆነው አመፅን በሃሳባቸው የሚኮመኩሙ ጥቂት በውጭ ሀገር የሚገኙ የደርግ ርዝራዦችና ደም የጠማቸው አሸባሪዎች መሆናቸውን ህዝቡ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ እነዚህ ሰዎች በመስቀል አደባባይ ግንቦት ሃያንና ገዥውን ፓርቲ ለመቃወም ሰልፍ ጠርተናል ነበር ያሉት።

ግንቦት ሃያ ያጎነፀፈውን ድል ባሸበረቀ ህያውነቱ ለመዘከር የወጣው ህዝብ ግን ስለ ሃሳብ ህልመኞቹ የሚያውቀው ነገር አልነበረም። ሁሉም ሰልፈኛ ሊባል በሚችል መልኩ ድህነትን ይራገማል፤ በስራም እንደ ሚያሸንፈው ለራሱ ቃል ይገባል፡፡ አብዛኛውም 'በትጥቅ ትግሉ ወቅት ለእኛ ሲሉ ውድ ህይወታቸውን ቤዛ ያደረጉ የህዝብ ልጆችን ዓባይን በመገደብ ልማታችንን በማፋጠን እንጂ፤ ሌላ በምን እንክሳቸዋለን?' ይላል፡፡ በቃ! በአደባባዩ ውስጥ የሚናኘው የተስፋ ነፋስ ይኸው ነበር።…እናም 'የእኛ አመፅ በድህነታችንና ልማታችንን በማይሹ ፅንፈኛ ዲያስፖራዎች ላይ ነው' ሲልም አደመጥኩ፡፡ ሁሉም አንድ ዓይነት ቋንቋ ይናገራል– 'ዓባይን ከማልማት የሚያግደን ምንም ኃይል የለም!' እያለ፡፡ በራሱ ተነሳሽነት በዚህ ዓይነት ሁኔታ መስቀል አደባባይ የተገኘው የልማት ኃይል የሆነው ህዝብ፣ ከበዓሉ ፍፃሜ በኋላም በሆታና በጭፈራ ወደ ቤቱ ሲመለሰ ታዘብኩ።

…እኔ ግን ግር አለኝ። “እናስ?…ሟርተኞቹ የቀለም አብዮተኞች የታሉ?”–ለራሴ ያቀረብኩት ጥያቄ ነበር፡፡ ሰልፈኛው ለዕለቱ ያለውን ክብር ከገለፀና ለግድቡ ግንባታም ድጋፉን ሙሉ በሙሉ ከቸረ በኋላም ቢሆን፤ የፌስ ቡክን ፌዘኞችና ይደግፈናል ያሉትን ህዝብ ፈልጌ አስፈልጌ አጣኋቸው፡፡…መቼም ነፍሱን ይማረውና እንደ ክቡር አርቲስት ዶክተር ጥላሁን ገሠሠ ሁሉም ነገር በግልፅ በሚታይበት በተንጣለለው መስቀል አደባባይ ውስጥ “ፈልጌ አስፈልጌ…ምንትስን ያጣኋት” እያልኩ በመርሴዲስ መኪና መዞር ያለብኝ አይመስለኝም፡፡ ህዝብ ለጠላውና በይፋ የሚያማልል አንዳች አጀንዳ ለሌለው ነገር መልፋት ከቶ ምን ፋይዳ ይኖረዋል?–ምንም፡፡

እናም ‘በኢንተርኔት ላይ ተፈራርመናል፤ ይህን ያህል ሺ.ህ ሰው ደርሰናል፣ ደጋፊ ህዝብ አለን…ወዘተ.’ እያለ ቱልቱላውን ሲነፋ የነበረው ያ የተቃውሞ ጎራ፤ እምጥ ይግባ ስምጥ ሊከሰት አልቻለም፡፡ ይደግፈኛል ያለው ህዝብም ቢሆን አደባባዮ ላይ አይታይም። ሃሳቡ ባዶ ነበር–ከወሬ በስተቀር ምንም የሌለው። እናም የሃሳባዊያኑ የቀለም አብዮተኞች ጥሪ፤ በህዝቡ ፍትሃዊና ሚዛናዊ አተያይ የሚሰማው ጆሮ አጥቶ ከውግዘት ጋር መክሸፉን አረጋገጥኩ፡፡…በወቅቱ ‘በቃ!’ ያሉት ህልመኞች ምናባዊ አብዮትም ያለ አንዳች ደጋፊ አደባባዩ ባዶ ሆኖ በዚህ መልኩ አበቃለት፡፡…

…እርግጥ ይህን የሁለት ዓመት ከሶስት ወር ትውስታዬን ያነሳሁት ያለ ምክንያት አይደለም–ሰሞኑን አንድነት የተሰኘው ሁከት አምላኪ ፓርቲ በተለያዩ የሀገራችን ከተሞች የጠራው ሰላማዊ ሰልፍ በህዝቡ ሚዛናዊ ፍርድ ሰው አልባ ሆኖ መና መቅረቱ ተመሳስሎብኝ እንጂ።…አዎ! አንድነት ፓርቲ ሰሞኑን በመንግስት አጀንዳዎች ላይ በመንጠላጠል የተቃውሞ ሰልፍ ያልጠራባቸውን ከተማዎች የሉም ቢባል ማጋነን አይሆንም። አዳማ፣ ሮቤ፣ ፍቼ፣ ጎንደር፣ መቐለ፣ …ወዘተርፈ። ሀገሪቱ ውስጥ የቀሩ ከተሞች ያሉ አይመስሉም። ኸረ እንዲያውም በግል እቤት ድረስ እየሄደ ‘ኑና የምለውን ነገር ስሙኝ’ ብቻ ማለት ነው የቀረው–አንዳች የሚሸጥና ህዝብን የሚማርክ የፖለቲካ ፖሊሲና ስትራቴጂ ያለው ይመስል። እርግጥ ፓርቲው ህገ-መንግሰቱ በሰጠው የመደራጀት መብት ተጠቅሞ ሰላማዊ ሰልፍ መጥራቱ ባልከፋ ነበር። መብቱም ነው። ግና ምን ያደርጋል!?..የሚመራበት ርዕዮተ-ዓለም ሁከት ቀመስ በመሆኑና ህዝቡም ባለፈው ተሞክሮው ይህንን የፓርቲውን የማይሽር ቁስል ያለበት የሚመስል አባዜን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ወደ ሰላማዊ ሰልፉ ሜዳ ብቅ ሊል አልፈቀደም። ነገሩ “ስንተዋወቅ አንተናነቅ” ዓይነት ይመስላል።…

ግና ፓርቲው ወትሮም ቢሆን በዜሮ ድምር ፖለቲካ የሚመራ በመሆኑ በየከተማዎቹ ሰላማዊ ሰልፍ የሚወጣለት ሰው ሲያጣ፤ “የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ” ዓይነት ምክንያቶችን ሲደረድር ይሰተዋላል–በመንግስት ላይ ጣቱን እየቀሰረ። እርግጥ በዚህ ፅሑፌ ፓርቲው በስሞተኛነት ‘እንዲህ ሆንኩ፣ እንዲህ አደረጉኝ…ወዘተ.” የሚለውን ልብ ወለዳዊ ትርክቱን

በመዘርዘር የውድ አንባቢዎቼን ጊዜ መሻማት አልፈልግም–ረብ የለውምና። እናም ለእኔ ስሜት የሚሰጠኝ ጉዳይ ህዝቡ በየከተማው ‘አውቅሃለውና እዛው በጠበልህ’ ያለው አንድነት ፓርቲ፤ ያለ አንዳች ፖለተካዊ አጀንዳ የገኘውን ፓርቲ ውጤታማ ስራዎች በማጠልሸት እንዲሁም የሌሉ ችግሮችን ለማራገብ በጠራው ሰልፍ ላይ ያገኘው ህዝባዊ መልስ ነው–ልክ በመግቢያዬ እንደጠቀስኳቸው የኢንተርኔት አብዮተኞች ላይ እንደወሰደው አሸማቃቂ ርምጃ። ከዚህ ባሻገርም ፓርቲው የዜሮ ድምር ፖለቲካ ስልቱ በህዝቡ እንደተነቃበት ያረጋግጣል። ይህ ሁኔታም የዜሮ ድምር ፓለቲካ ስልት ውጤቱ ያው ዜሮ መሆኑን ያመላከተ ነው ማለት ይቻላል።…‘እኔን ዜሮ ያድረገኝ ልበል እንዴ?!’–ልጄ!…እኔ ምን በወጣኝ! እዛው እነርሱው በጠበላቸው ራሳቸው ይቻሉት እንጂ!…እናንተዬ ‘ዜሮ ነበርክና ዜሮ ትሆናለህ’ ያለው ማን ነበር–መቼም አንድ መሆን ያቃተው የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ሊሆኑ አይችሉም። እርሳቸው ይሆኑ እንዴ?…ቂ.ቂ.ቂ….

ያም ሆነ ይህ እዚህ ላይ የተነሳሁበት ርዕሰ ጉዳይ ለውድ አንባቢዎቼ ግልፅ ይሆን ዘንድ፤ ከአንድነት ፓርቲ እንቅስቃሴ አኳያ የዜሮ ድምር ፓለቲካን ምንነት በማሳየት፤ ፓርቲው ለህዝብ ተሸጦ የሚያሳምን ምንም ዓይነት አጀንዳ ሳይኖረው ያለ አቅሙ ዘሎ ሰልፍ በመጥራት የተለመደው ዜሮነቱ እንዴት በተግባር እንደተረጋገጠ ለማመላከት እሞክራለሁ። አብረን እንዝለቅ። … ታዲያ እኔ ጋር በጉዳዩ ዙሪያ አብረን ስንዘልቅ የኋሊት የዛሬ ስምንት ዓመት ገደማ እንዲህ እወስዳችኋለሁ።…ምርጫ 97።…የእነ አንድነት ፓርቲ የዜሮ ድምር ፖለቲካ አልፋና ኦሜጋ አስተሳሰብ በገሃድ የታየበት ወቅት።…እንደሚታወቀው የዜሮ ድምር ፖለቲካ ጨዋታ (Zero sum game politics) ሁሉንም ፈልጎ ሁሉንም የማጣት ተግባር ነው። አንዳንዶች የኪራይ ሰብሳቢነት አባዜን የዜሮ ድምር ፖለቲካ ውጤት ነው ይላሉ። እርግጥም ይህ አባባል እኔንም የሚያስማማኝ ነው። ምክንያቱም የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ- ኢኮኖሚ ስርዓት በነገሰበት ሀገር ውስጥ አንድ ቡድን ወይም ግለሰብ የሚያገኘው ጥቅም የሌሎችን መብት ዘግቶ በመሆኑ ነው።

ሀገራችን በአሁን በምትገኝበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ልዩነትን በሠላማዊ መንገድ መፍታት፣ መቻቻልን መሰረት ማድረግ እንዲሁም አንዱ ሲያገኝ ሌላው በልማታዊ ውጤቱ መጠን የሚያገኝበት ሁኔታ በመኖሩ ነው፡፡ ዳሩ ግን በዜሮ ድምር ውጤት አሰላለፍ ፤ አንዱ ሲያገኝ የሌላው የማግኘት መብት በዚያው መጠን ይዘጋል፡፡ እናም በዚህ የጥሎ ማለፍ ውድድር ውስጥ መቻቻል የሚባል ነገር ከቶውንም ሊታሰብ አይችልም፡፡ ታዲያ ውድድሩ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችን ውስጥ የተንሰራፋ ከሆነ፤ ፖለቲካው ራሱ የዜሮ ድምር ጨዋታና ፀረ- ዴሞክራሲያዊ ከመሆን የዘለለ ዕጣ ፈንታ ሊኖረው የሚችል አይመስለኝም፡፡ በመሆኑም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችን ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ የዜሮ ድምር ውጤት የጥሎ ማለፍ ውድድር እንዲዘጋ፣ በአስተሳሰቡ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች እጆቻቸው ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

ይህን አባባል የጉዳያችን ባለቤት ከሆነው አንድነት ፓርቲ አኳያ ልንመለከተው እንችላለን። ፓርቲው በምርጫ 97 ወቅት በቅንጅት ነውጠኛ አመራር ማዕቀፍ ስር ሆኖ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳድሮ አዲስ አበባ ላይ ማሸነፉ አይዘነጋም። ይሁንና ያሸነፈበትን ክልል ተረክብ ሲባል አሻፈረኝ ይላል። ምክንያቱ ደግሞ በሌሎች ቦታ ያሸነፍኩትም እኔ ነኝ የሚል ሁሉንም የማግኘት አባዜ ነው– ያልዘራውን የማጨድ ፍላጎት። ታዲያ ላም ባልዋለበት ቦታ ኩበት መልቀም አይቻልምና የተጣማሪው ፓርቲ ፍላጎት ያመራው ወደ ጎዳና ላይ ነውጥ ተግባር ፀረ-ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ነበር።

ይህም ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ ከመፍታት ይልቅ የጠብ በርን የመናፈቅ፣ ከመቻቻል ይልቅ በገሃድ የሁከት አካሄድን መከተል ብሎም የሃቅን መንገድ በመተው የቅጥፈት አራማጅ በመሆን ፀረ-ዴሞክራሲያዊነትን የመሻት ፍላጎትን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው። ግና በስተመጨረሻ በቅንጅት ውስጥ የነበሩት አመራሮች ስልጣንን እንደ ህዝብ መገልገያ መሳሪያ ሳይሆን እንደ መጠቀሚያ ስለሚመለከቱት ሊስማሙ አልቻሉም። ወትሮም የኪራይ ሰብሳቢነት ፀረ–ዴሞክራሲያዊ አካሄድ በመርሆዎች ላይ በመስማማት ሊሰራ ስለማይችል፤ አንድነት ያለበት ቅንጅት የተሰኘው የነውጥ አመራር ቡድን እርስ በርሱ ቢባላ የሚገርም አይሆንም። እናም ሁሉም ሁሉንም የማግኘት ፍላጎቱ አይሎ ተበታተኑ። ሁሉንም ሽቶ ሁሉንም የማጣት የዜሮ ድምር የፖለቲካ ጨዋታ ይሏል እንዲህ ነው።…

የዜሮ ድምር ፖለቲካ ጨዋታ ሌላኛውን ገፅታ 'ከእኔ ወዲያ ላሳር' በማለት ሌሎችን ማጣጣልና ማናናቅ ነው። ታዲያ ይህን ዕውነታ ከአንድነት አኳያ ስንመለከተው ፓርቲው በአጠቃላይ፣ አመራሮቹ በተለይ የጉዳዩ ሰለባ ሆነው እናገኛቸዋለን። ጥቂት አብነቶችን ላንሳ– በምርጫ 2002 ወቅት ያከናወነውን።

እንደሚታወቀው አንድነትና ተጣማሪዎቹ የፀረ-ህገ-መንግስትነትን ካባ ደርበው የኢ-ዴሞክራሲያዊነት ተመሳሳይ ዜማን እያቀነቀኑ በመገኘታቸው፤ ሚዛናዊውና ፍትሐዊው የሀገራችን መራጭ ህዝብ አጠቃላይ እርስ በእርሱ የማይተማመነውን የቡድኑን ስብስብ ዳግም ወደ ፓርላማ ዝር እንዳይል በካርዱ ቀጥቷቸዋል። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ መድረክ በተሰኘው የእሳትና ጭድ ስብስብ ውስጥ የተካተቱት አንድነትና ተጣማሪ ፓርቲዎቹ፤ 'ያለ እኔ ፈቃድ ልማትን፣ ሰላምንና ዴሞክራሲን ያጎናፀፈችን ህገ- መንግስት ቀዳድዳችሁ ልትጥሉ እንዲሁም የእኔን ሉዓላዊ መብት በመግፋት በውጭ ሃይሎች አማካኝነት የስልጣን እርካብን ልትቆናጠጡ በየኤምባሲው አርቲ ቡርቲ ወረቀት ይዛችሁ ስትዞሩ ተመልክቻችኋለሁ' የሚል እንደነበር አይዘነጋም።…መቼም ለአንድ ለሚያመዛዝን ወገን ከዚህ በላይ ውርደት ያለ አይመስለኝም። እውነትም አንድ የፖለቲካ ፓርቲ

'ይመርጠኛል' በሚለው ህዝብ እንዲህ ከመብጠልጠል በላይ ከቶ ሌላ ነገር ምን ይመጣበታል?–ምንም።

አንድነትና አመራሮቹ ግን ከዚህ ስህተታቸው ከመማር ይልቅ ያመሩት ወደ ሌላ ፀረ-ህገ-መንግስት ተግባር ነበር–አሁንም 'ለኢትዮጵያ ህዝብ የምናስበው እኛ እንጂ ሌላ አይደለም' በሚል የዜሮ ድምር ጨዋታቸው እየተመሩ የመካከለኛው ምስራቅና የሰሜን አፍሪካውን አብዮት በግድ ከኢትዮጵያ ጋር አጣብቀው በመስፋት ሀገራችን ውስጥ እንዲቀጣጠል በቀቢፀ-ተስፋ እየተመኙ ከህዝቡ ይሁንታ ውጪ በአቋራጭ ስልጣንን ለማግኘት መቋመጥ። ታዲያ ያ ወቅት አንድ አመፅ ሌላ ሀገር ውስጥ ሲቀሰቀስ የስሜት ህዋሳታቸው አንዳች ዕፅ የወሰዱ ያህል የሚነቃቃው የአንድነት ሰዎች፤ በጉዳዩ ዙሪያ በአስገራሚ ሁኔታ ወደ 'ትንቢት ተናጋሪነት'ም ተቀይረው ነበር። እንዲያውም አንዳንድ ወገኖች ይህን የፓርቲውን በባዶ ሜዳ ላይ 'እኛ ነን አዋቂዎች' ባይ አመራሮችን አስቂኝ ሁኔታ ተመልክቶ የ8ኛው ሺ የከሰሩ መፅሐፍ ገላጮች እስከማለት ደርሰዋል።…

…ያም ሆነ ይህ እስቲ ለቅምሻ ያህል የፓርቲውን አመራሮች ትንቢት ተናጋሪነት በጥቂቱም ቢሆን እንካችሁ ልበል።…ግና ከማን እንጀምር?...ለነገሩ ይህ ጉዳይ አያሳስበንም–"ሁሉን አወቆቹ" ሁሉም የፓርቲው ትንቢተኞች አንድም ሁለትም ናቸውና–"የአያ ነውጤ መንትያ ልጆች" እንዲል አንድ ወዳጄ።…እስቲ በቅድሚያ ዛሬ በህግ ጥላ ስር ካሉት አቶ አንዱዓለም አራጌ እንነሳና ማሳረጊያችንን"…የቦይ ውሃ ናቸው" ተብለው በሌላ የፓርቲው ተሰንጣቂ አመራር ወደ ተዘለፉት የፓርቲው ወረፈኛ መሪ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ላይ እናድርግ፤ የማወጋችሁ አብነታዊ ቅምሻ ብቻ ነውና።…

…ፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ያለበትን ቦታ እያሸተቱ 'በድንኳን ሰባሪነት' መገኘት የማይሰለቻቸው የፓርቲው አመራሮች፤ አብዛኛዎቹ በሶስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ወቅት በቅንጅት ነውጠኛ አመራሮች ስር ታቅፈው 'ሁከት' የተሰኘች ፍቅረኛቸውን ለማግኘት ሲሉ የአደባባይ ላይ ነውጥን ቀምረው መንቀሳቀሳቸው የሚዘነጋ አይደለም። ታዲያ እኔም ሆንኩ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደምናውቀው የዛሬ ስምንት ዓመት ገደማ አዲስ አበባ ውስጥ በቅንጅቱ ነውጥ አከፋፋይነት ስድስት ቁጥር ማለያ ለብሰው ሲጫወቱ እንደነበሩ የማንዘነጋቸው የአመፅ አጋፋሪው አቶ አንዱዓለም አራጌ፤ 'በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ መካከለኛው ምስራቅና ሰሜን አሜሪካው ዓይነት ህዝባዊ ማዕበል ካልተነሳ እንትፍ… እንትፍ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል' ሲሉ ነበር። ከንግግር አልፈውም በስራ ላይ የተጠመደውን የሀገራችንን ህዝብ ለአመፅ በመቀስቀስ ግልፅ የሆነ ህግ የመፃረር ተግባርን ሲከውኑ ነበር።

ትናንት “ዳግም የአመፅ ስራ አላከናውንም” ብለውና ምህረት ጠይቀው ከእስር ቤት የተለቀቁት አቶ አንዱዓለም ፤ የሚቋምጡለት ነውጥ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊከሰት የሚችልበት ነባራዊ ሁኔታ በሩ የተከረቸመ መሆኑ እንኳን እንዲገባቸው የሚፈልጉ አይደሉም— ዓላማቸው ህገ-መንግስቱን በመጣስ ወደ ስልጣን የሚወስድ ማናቸውንም ዓይነት የሁከት መንገድ መፍጠር ነበርና። ግና እርሳቸው ምንም ያልሙ ምን፤ ሰውዬው ህገ-መንግስቱን ተመርኩዞ በተረቀቀውና የህዝቡ ወኪል በሆኑት የተወካዩች ምክር ቤት አባላት በከፍተኛ ድምፅ ባፀደቁት የፀረ-ሽብር አዋጅን ተላልፈው በመገኘታቸው እንደ ማንኛውም ዜጋ በሀገራችን ፍርድ ቤቶች ጉዳያቸው ሲታይ ቆይተው የተከሰሱበትን ወንጀል መከላከል ባለመቻላቸው የህግ የበላይነት ተግባራዊ እንዲሆንባቸው ተደርጓል።

በምርጫ 2002 ወቅት ‘ቢጤዎቼ ሲናገሩ እኔስ ለምን ይቅርብኝ’ ብለው ነው መሰል፤ ቅድም እንደነገርኳችሁ በተሰንጣቂ የፓርቲው አባላት “የቦይ ውሃ፣ የቦይ ምንትስ” እየተባሉ ማንነታቸው በየመገናኛ ብዙሃኑ እንደ ጣቃ ሲተረተርላቸው የነበሩት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ እንኳን “የፖለቲካ ፓርቲዎች መዳከም የሰሜን አፍሪካን ዓይነት ህዝባዊ አመፅ ለማነሳት አያግደውም” ማለታቸውን ዛሬ ላይ ሳስበው ድንቅ ይለኛል። ምክንያቱም ተሰንጣቂው የአንድነት አመራር እንዳሉት ዶክተሩ “የቦይ ውሃ” ስለሆኑ ማንም ወዳሻው የሚነትታቸው ከሆኑ፤ ነገ ደግሞ ሌላ የሰሙትን ነገር አለመናገራቸውን ማንም ሰው እርግጠኛ ሊሆን ስለማይችል ነው።

እርግጥ ዶክተሩ ተሰንጣቂው ሰውዬ እንዳሉት በፓርቲው አመራሮች እንደ ፔንዱለም ከወዲያ ወዲህ እየተወዛወዙ አንድነት የተሰኘውን የሁከት ማቀነባበሪያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የነውጥ ተንባዮች ቡድንን እንዴት እንደሚመሩት ለእኔ ግልፅ አይደለም። ሆኖም አንባቢዎቼ ግን በ‘ከእኔ ወዲያ ላሳር’ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ስሌቱ ፓርቲው ተግባሩን ቀይሮ ወደ ትንቢት መናገሪያ ቤተ-መቅደስነት መገንዘባችሁ የሚቀር አይመስለኝም። ለነገሩ የያኔው የዶክተሩ አባባል የፓርቲው አመራሮች በፀረ-ህገ-መንግስታዊ ብረት ድስት ውስጥ ተቀቅለው የበሰሉ መሆናቸውን አፍ አውጥቶ የሚናገር ነው—“ከዝንጀሮ ቆንጆ ማንን ይመርጧል” እንዲል የሀገራችን ሰው፡፡

አዎ! ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ ቀደም ሲል ከጠቀስኳቸው የአንድነት ፓርቲና የአመራሮቹ ጥቂት አብነታዊ ማንነቶች በመነሳት አንድ ወሳኝ ሃቅን መረዳቱ አይቀርም። ይኸውም ፓርቲውና አመራሮቹ በዜሮ ድምር ፖለቲካ እየተመሩ ስልጣንን ያለ ህዝብ ይሁንታ ለማግኘት፣ ከፍ ሲልም ህዝቡን በመናቅና ህገ-መንግስቱን በመጣስ ላይ ተሰማርተው ሲንቀሳቀሱና እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ነው። ይህ ድርጊታቸውም ለይስሙላ ህገ-መንግስቱን አክብረን በሰላማዊ ትግል እንደ ፓርቲ እንሰራለን እያሉ፤ በተነፃፃሪው ጭልጥ ባለ የፀረ-ህገ-መንግስታዊ ባህር ውስጥ መስመጣቸውን የሚያመላክት ነው።

ፓርቲውን አደቁኖ ያቁሰሰው ሌሎችን የማጣጣልና የማናናቅ የዜሮ ድምር ጨዋታው በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። ፓርቲው በቅርቡ "እግር ራስን አያክም" የሚለውን ይትብሃል 'ከኔ ወዲያ ማን አለ' በሚል የዜሮ ድምር ፖለቲካው ይትብሃል ተክቶ መድረክ የሚባለውን የማይተማመኑ ባልንጀሮች ስብስብ 'ካልገመገምኩህና ካልመራሁህ ሞቼ እገኛለሁ' ሲል ተመልክተነዋል። ለነገሩ አንድነት በእናት ፓርቲው ላይ ጥናት አካሂዶ ለመገምገም የተነሳው ከመሬት ተነስቶ አለመሆኑን ውድ አንባቢዎቼ እንድትገነዘቡልኝ እሻለሁ። ምክንያቱም በእኔ እምነት በመድረክ ውስጥ ያሉት ሁሉም ፓርቲዎች የዜሮ ድምር ፖለቲካ ተጫዋቾች በመሆናቸውና ሁሉም 'አዋቂዎቹ እኛ ነን' ባዮች ስለሆኑ፤ ድንገት አንዱ ፓርቲ ሳይታሰብ መድረክን ልገምግመው በማለት የበላይነቱን ካሳወቀ አንድነት ውሃ በላው ማለት ነው። እናም ከእርሱ አንፃር እንደ ተውሳክ የተጣባውን ይህን "ጨዋታ" መተወኑ ትክክል ነው። እርግጥም ፓርቲው እንዲህ ካላደረገ ምኑን 'አዋቂ' ሆነው?...'እቴ እኔን አዋቂ ያድርገኝ!' አሉ ጎረቤታችን እማማ እታገኝ።...ያም ሆነ ይህ ግን ፓርቲው መድረክ ውስጥ እያለ የሌለ ፓርቲ ይሁን አሊያም ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ እንኳንስ ለእኔና ለአንባቢዎቼ ቀርቶ ለራሱም የገባው አይመስለኝም–ሁለት እግር አለኝ ብሎ ሁለት ዛፍ ላይ እየወጣ ነውና።

የዜሮ ድምር ፖለቲካዊ ጨዋታ ሀገራዊና ማህበራዊ ጥቅም የሚያስገኙ ጉዳዮችን እንደ ተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ ነው የሚፈራቸው–ሁሉንም ነገር የሚመለከተው ከራሱ ተጠቃሚነት አኳያ ብቻ ነውና። ታዲያ አንድነት ፓርቲ ከዚህ አንፃር የፀረ-ሽብር ህጉን "ከፍተኛ አመራሬን አቶ አንዱዓለም አራጌንና የምክር ቤት አባሌን አቶ ናትናኤል መኮንንን አሳጥቶኛል" በማለት ከራሱ በስተቀር ለሀገራዊ ጥቅም ደንታ ቢስ መሆኑን በግላጭ ነግሮናል። እንግዲህ ልብ በሉ!...ማንኛውም ሰው በህግ ፊት እኩል ነው። እናም አንድ አዋጅ ወይም ህግ የሚወጣው ለሁሉም ዜጎች ነው–ለፖለቲከኛውም፣ ለሙዚቀኛውም፣ ለመሃንዲሱም፣ ለሀኪሙም፣ ለቀዳሹም፣ ለተኳሹም...ወዘተርፈ።

ግና አንድነት ፓርቲ የአዋጁን ሀገራዊ ፋይዳ ወደ ጎን በማለት 'አዋጁ አመራሮቼን ነጥቆብኛል' ብሏል–በዚህም ምክንያት ህጉ መሰረዝ እንዳለበት በማተት። በእኔ እምነት ይህ የፓርቲው አስገራሚ ከሀገር በፊት ራስን የማስቀደም ኪራይ ሰብሳቢነት ምልከታ ሁለት አንድምታዎች ያሉት ነው። አንደኛው 'እኛ እንደፈለግን ከህግ ውጪ መሆን እንችላለን' የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አዋጁ በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ እንዳይፈተፍቱ ያገዳቸውን የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎችን አጀንዳ ተቀብሎ መጮህ ነው።

እደሚታወቀው በህግ ካለተደነገገ በስተቀር በየትኛውም ሀገር ውስጥ የሚኖር ዜጋ የህግ የበላይነትን በመፃረር እንዳሻው ሊኖር አይችልም። የዜጎች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በህግና ስርዓት የሚመራ ካልሆነ የትኛውም ወገን የመኖር ዋስትና ሊኖረው አይችልም። የመኖር ዋስትና በሌለበት

ሀገር ውስጥ ደግሞ ሰላምና መረጋጋት ይጠፋና እንደ ሰው ለመንቀሳቀስ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ይደረሳል። መብት ሰጪና ነሺ ጉልበተኞች ይሆናሉ። ጉልበተኞቹም ሌሎች ዜጎችን እንዳሻቸው በማድረግ የባሪያና ሎሌ ስርዓት መፍጠራቸው አይቀሬ ነው። እናም ይህን ሁኔታ ለመከላከልና ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን የህግ የበላይነት መኖር የግድ ይላል። እናም አንድነትም ይሁን የትኛውም ሰላማዊ ፓርቲ ነኝ የሚል የፖለቲካ ክንፍ ህግ ባለበት ሀገር ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ከህግ በላይ ሊሆን አይችልም።

ታዲያ እዚህ ላይ አንድነት ፓርቲ አመራሮቹ በተከሰሱበት የሽብርተኝነት ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው ምክንያት በሀገሪቱ ህግ መሰረት በህግ ጥላ ስር ስለዋሉ፣ የግድ ከህግ በላይ ሆኜ ህግን ሽራለሁ ብሎ የመነሳቱ ስህተት ዋነኛ ምክንያት ይኸው ይመስለኛል። ምክንያቱም አመራሮቹ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙት በተከሰሱበት የሽብርተኝነት ወንጀል እንጂ በፖለቲከኝነታቸው ባለመሆኑ ነው። ለነገሩ ሀገራችን ውስጥ የታሰረ ወንጀለኛ እንጂ ፖለቲከኛም ይሁን ጋዜጠኛ የለም።

ያም ሆነ ይህ ግን እርግጥም ፓርቲው ሰዎቹ ‘አመራሮቼ ናቸው’ የሚል ከሆነ ማድረግ የነበረበት ግለሰቦቹ በወንጀል በተከሰሱበት ወቅት ጥፋተኛ አለመሆናቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃ በማቅረብ በፍርድ ቤት ነፃ ማስባል ነበር። ከዚህ ውጪ ሰዎቹ በፍርድ ቤት በአሳማኝ የሰውና የሰነድ ማሰረጃ ጥፋተኛ ተብለው ካበቁ በኋላ፣ ወንጀላቸውን በመደባበቅ ‘አዋጁ አመራሮቼን ስላሳጣኝ በፊርማ አሰርዘዋለሁ’ ማለት በየትኛውም መንገድ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር፣ ‘ህግን ደፍጥጠን እንደፈለገን ብንንቀሳቀስ ማን ከልካይ አለብን!’ የማለት ያህል ስለሆነ ቢታረም በጄ ነው ባይ ነኝ። ግና ፓርቲው የዜሮ ድምር ፖለቲካ ጨዋታ አብሮት ተወልዶ ያደገ በመሆኑ ይህን ስህተቱን ከማረም ይልቅ ፓርቲውን ቢያፈርሰው የሚቀለው ይመስለኛል። ምክንያቱም ሰሞኑን በሀገራችን ውስጥ ባሉት ከተሞች የጠራውና ህዝቡ ‘ስንተዋወቅ አንተናነቅ’ በማለት ዝር ሳይል የቀረባቸው ሰልፎች የእሳቤው ቀጣይ ክፍል በመሆናቸው ነው—ጨዋታውን በተግባር ከውኖ የውጤቱን ዜሮነት ያረጋገጡም ጭምር። አበቃሁ።